# ከህይወት በመማር :- መውጫችሁን ፈልጉ !!

ከዶ/ር መንጌ አዱኛ

ለነፃነት ሲሉ ለወያኔ ጥይትና እስር ሰላባ ለሆኑት ማስታወሻ

---

**ሲጀምሩ :-**

ያልተባረከች ቀን ወያኔዎች መጡና:
ሲያተራምሷት የአበሻን መዲና:
ዝንተ ዓለም ለመግዛት ወጥነዋልና።

**ከዚያም:-**

ከገቡ ቀን ዕለት ዜጋን ሁሉ አምሰው:
መሌው ባንዲራዋን በጨርቅ አመሳስለው:
ከእንብርቷም በላይ ኮከብ ቢጤ አኑረው:
ነባር ድርጅቶችን በሙሉ አፍርሰው:
ያገር ተራካቢን ለስደት ዳርገው:
የዩኒቨርስቲ ምሁራንን ከሥራ አፈናቅለው:
ፕ/ር አስራትን እወህኒ ቤት ከተው:
በፍራንኮ ቫሉታ ሸቀጥ አስገብተው:
ኦነግንም በ19 ወንበር እንዲሁ አጭበርብረው:
ወንበርና ሥልጣን ለራስ አመቻችተው:
የኢትዮጵያን ታሪክ ከ300 ዓመት አድርገው:
ሰበካ ጀመሩ ከህዝብ መኃል ገብተው:
መጀነን ቀጠሉ በአገር ተንበሻብሸው።

**ተነሱ አሉን :-**

ሁላችሁም ተነሱ ፍቅራችን ይጥና:
ትግራይን መገንጠል ትተነዋልና:
ቤተመንግሥት ገብተን ያላንዳች ፈተና:
በአዲሳባም አየር እንናፈስና:
በጉልበት በኃይል በመጠቀምና:
የደርግም ስልት ቢሆን ሳይቀርብን አፈና:
ማንበርከክ መቻል ነው ከባሌ እስከ ጣና:
አለዚያ ይህ ሕዝብ አይቻልምና።

**ሲለያዩን :-**

ለሕዝብ ያለንን ድጋፍ ይይልን ሰው ሁሉ:
ብለው እየዘፈኑ በውል ሲያታልሉ:
በአልባኒያ እምነታቸው ሳይቀር እየማሉ:
በዘር መከፋፈል ስልታችን ነው አሉ:
ወደብ አልባ አድርገው ኢትዮጵያን ከለሉ።




**ማጭበርበር በየፈርጁ :-**

ዘፈን ተዘፈነ ከበሮም ተመታ:
እልል በሉ አሉን በትግሪኛ እስክስታ:
በጉራጌ ስልጢ በኦሮሞ ረገዳ:
በሱማሌ በኮንሶ እንዲሁ በወላይታ:
ሁሉን ውጡ ብለው ፈጥረውብን ጋጋታ:
እነሱ ሊሆኑ አለኝታ መከታ:
ይህ ሁሉ ጥጋባቸው ኋላ ግን ሊገታ:
ከወረቱ ኋላ ከወያኔ ድንፋታ:
ጦርነትን አቀጣጥሎ መለስ በሁካታ:
በባድመ ሰበብ ኢሳያስ ሊመታ:
መቶ ሺህ አስጨርሰው በትንሽ ኮረብታ:
ለተከፈለው ደም ካሳቸው ውለታ:
ዘ ሄግ (Hague) ላይ እጅ መንሻ አስርተው ካርታ:
ዛለአንበሳ ባድመን አቅርበው ስጦታ:
መስቀል አደባባይ ውጡ አሉ በእልልታ:
ማጭበርበር ይሉታል ይቺ ነች ጨወታ:

**ይገዙታል ህዝቡን:-**

ትልማ አልማ አልማን አደራጅተው:
ብዝበዛውን ገቁበት ሁሉን ተቆጣጥረው:
ዳያስፖራውም ሳይቀር እንዲሁ አጭበርብረው:
ባገር በልማት ስም ምለው አስመስለው:
ከውጭ አገር ህግጋት ሰነድ አስገልብጠው:
የቤት መሥሪያ ቦታ ለድለላ አቅርበው:
የእርሻ ቦታን መሬት ከገበሬ ነጥቀው:
ለፈለጉት ማህበር መሬት አደላድለው:
ባለሥልጣናቱም በንግድ ተሰማርተው:
ሚጋ አዜብ ኤፈርት ምኑን አስቀርተው?
መብራት ኃይልን ደግሞ ለቦንድ አጫርተው:
ለሜርሴዲስ ሃመር ለማሽከርከሪያቸው:
ቀለበት መንገዶችንም አሰራንልህ ብለው:
አዜብ ሚሊዮነር ህንፃ አከራይተው:
የማይፈልጉትን በሙስና ከሰው:
ለኢንተርነት ቁጥጥር ቻይናዎችን ቀጥረው:
የፕሬስን ነፃነት በውን አጨልመው:
ቻሪቲ ህግ ብለው ዓለምን አስደንግጠው:
ሬዲዮ ቴሌቪዥን እንዳሻቸው አድርገው:
ይገዙታል ህዝቡን አፍነው ጨቁነው።

**እድሜያቸውን ማራዘም :-**

ለሚመጣው ሁሉ እየሆንህ ተገን:
እንደግፍሃለን በህይወት እስካለን:
ለኛ የሚመቸውን ሁሉን ነገር አድርገን:
ያገሪቷን ንብረት ሽጠን አካፋፍለን:
ለዓለም ባንክ ይሁን ሌላ በልማት ስም ዋሽተን:
ለሱዳንም ቢሆን መሬት ቆርሰን ሰጥተን:
ለደጋፊዎቻችን በምርጫ አሳብበን:
እናም ለገበሩልን ሥልጣን አስጨብጠን:
የካድሬ ጆሮ-ጠቢ(ተደራቢ) ከሥር አሳማርተን:
የጦር ኃይሉን ሁሉ እኛው ተቆጣጥረን:
የዓግአዚን ጦር በውል አሰማርተን:
የነጋዴውንም ላይሰንስ ስንፈልግ ቀምተን:
የካመቹትን ሸቀጥ በሐራጅ አስሸጠን:
ለውጭውም ፕሬስ መግለጫ አሰራጭተን:
መሌ ነፍስ ገዳዩን (ምላሰኛውን) አንበሳ ነው ብለን:
በሱማሌም ቢሆን ጦርነት አውጀን:
ለማሳሳቻ ይሆን ዘንድ ብርቱካንን አስረን:
ትንሽ ቆየት ብለን በኩዴታ አሳበን:
ተቃዋሚዎቻችንን ቃሊት አስቀምጠን:
ቢሮዎቻቸውንም በየቦታው ዘግተን:
ከምርጫው በፊት ሳይቀድሙን ቀድመን:
ይህ ሲያልፍ ደግሞ ዘዴ ቢጤ ፈላልገን:
እድሜያችንን ማራዘም በዚህም በዚያ ብለን:
ፎርሙላው ከሰራ እኛ ምን ቸገረን።

**ይዘልቁ መስኳቸው:-**

ጥቂት ያልገባቸው እናም የገባቸው:
የአገርን ጉዳይ በጥቅም ለውጠው:
ያላንዳች ጥያቄ ወያኔን ደግፈው:
በየኤምባሲዎች ድግስ አስደግሰው:
ለወያኔ ባለሟል ለአገልግሎት ታጭተው:
በነ አይጋ-ፎረም መጣጥፍ አቅርበው:
ከርሳቸውን ለመሙላት በርግጥም አስበው:
ተነስቷል ሊጓዙ ይዘልቁ መስኳቸው።

**ወህኒ ቤት ታጎሩ (ጠቋሚ):-**

አንድ አሥር እርምጃ እንደው ሳይራመዱ:
መጋጨት ጀመሩ በጥቅም እያበዱ:
ማሰብ ተስኗቸው የተመሰጣጠሩ:
በውሸት በሐሰት ሲመሰካከሩ:
ሲወነጃጀሉ ሲደነቋቆሩ:
በወያኔ ታፍሰው ወህኒ ቤት ታጎሩ።

**የብርቱዋ ቃሌ:-**




ወያኔ አዘቅት ውስጥ በለበት ሁኔታ:
ፀረ-ህዝብ ፀር-አገር ድርጊቱን ሳይገታ:
ሌላውን መኮነን ሁካታ ጫጫታ:
እየገጠመውም የሕዝብ ነቀፌታ:
ብርቱካን ሚደቅሳም ገብቷት ይህ ሁኔታ:
የወያኔን ውድቀት ላፋጥንለታ:
ቃሌ ነው የኔ ህግ የህዝብ አመኔታ:
ለወገን የሚበጅ ትንሹ ውለታ:
መርሳት የማልችለው ለሰከንድ ላንዳፍታ:

**.....የብርቱዋ .....**



የወያኔ ሥርዓት ከስሩ  እስኪመታ:
መቸር እችላለው ይህንን ስጦታ:
ኢትዮጵያን አትርሷት ባምላክ በኔ ጌታ:
ብላ አስማለችን ካለችበት ቦታ:
እኛም ቁርጠኞች ነን እሷ እንድትፈታ:
ሁሉም ነፃ ይውጣ ከአረምኔዎች ጨወታ:
ትግሉ ይቀጥል በተሻለ  ሁኔታ:
ህዝባችን ይላቀቅ ከመለስ/በረከት ድንፋታ።

**በሰፈሩት ቁና:-**

ወያኔ ተጨንቆ ቀኑ ጨልሞበት:
የወትሮ ዘረፋውን አሚሙቆ ይዞት:
በረከትና መሌው ቅጥፈቱን ቀጠሉት:
እብደት ብሶባቸው ራስንም በመሳት:
በምርጫ አስታክከው ሕዝባችንን በጥይት:
አጣሪውን ቡድን ሪፖርት አስቀይረውት:
በግንቦት(7) አሳብበው ሌላውንም በእስር ቤት :
ዘር ማጽዳት መስኳቸው መቆያው መድኃኒት:
አመኒስቲ ጄኖሳይድ ጉዳዩን ዘግበውት:
መለስና በረከት ቢያዩትም በንቀት:
በሰሩት ወንጀል ላይጠየቁበት:
እውነትን መለወጥ በማይቻልበት:
ክፍለ ዘመናችንን ሳይገነዘቧት:
እንደነ ሚሎሶቪች ተይዘው ሊገቧት:
በዓለም ፍርድ ቤት ህግና ሥርዓት:
በቅርብ ልናይ ነው የወያኔን የሞት ሞት:
በፈጸሙት ወንጀል ለረዥም ዓመታት:
መቀጠል አይችሉም በለመዱት ቅጥፈት:

በምድር ብቻ ሳይሆን በላይኛውም ቤት:
ይጠብቃቸዋል የእግዚአብሔርም ቅጣት:
በሰፈሩት ቁና የሚሰፈሩበት።

**ሐቅ መች ይሰወርና:-**

ምድረ ሆዳም ሁሉ በሄደበት ጎዳና:
ተሰብሮ መውደቁ አይቀርለትና:
የወደቁም አሉ ሲሉ ደፋ ቀና:
መጽሐፍ ቅዱስ ሰበካም ጀምረዋልና:
ኢሳያስም በቅርቡ ተናዘዋልና:
ውሎ ይደር እንጂ ሐቅ መች ይሰወርና:

**አእምሮን የተሸከማችሁ:-**

አሁንም በመዝረፍ መስመር ላይ ያላችሁ:
አእምሮን ያክል ነገር የተሸከማችሁ:
ወያኔን አዝላችሁ ያንበሸበሻችሁ:
በትግሉ ጎራ ያልተሰለፋችሁ:
እኔ ምን ቸገረኝ አርጉት እንዳሻችሁ:
በኃይማኖት ሥም ሰበብ ፈጣጥራችሁ:
የዜግነት አደራን ለጸሎት (ብቻ) ሰጥታችሁ:
ያላንዳች ተዋፅኦ እጅ አጣምራችሁ:
ተነሱ ንቁ እንጅ ለወደፊታችሁ:
ከነታምራት ላይኔም ትምህርት ወስዳችሁ:
የእነ ስዬም ጉዳይ የተዋጠላችሁ:
እንደ ዶ/ር ነጋሶ ዘግይቶም ቢገባችሁ:
እንደ አቶ ልደቱ ክህደት ሳያምራችሁ:
ምሳሌዎች ሞልተዋል መማር ከቻላችሁ:



እንደ ኢንጂነር ኀይሉ ዝንፈትን አውግዛችሁ:
ሥርዓትን አስፍኑ (ለልጆቻችሁ)የዘለዓላማችሁ:
ዲሞክራሲ ይስፈን (ለአገራችን) ለኢትዮጵያችሁ።




**የከፋፋዮች ሽንገላ:-**

በዘር ኃይማኖት በድንበር ከለላ:
ሶፎመር ፋሲሊደስ ሐረር ግንብ መቅደላ:
ጋምቤላ ኦሮሞ ትግሬ ላሊበላ:
የማይጠቅመንን የገዢዎች ፍተላ:
ጭራሽ ማስቀረት ነው ክፉውን ብጠላ።

**ኦባማ ይመስክር:-**

የኤውሮፓ ዩኒየን የኢኮኖሚ ትብብር:
ዘዴውና ስልቱን በማየት በመማር:
ረሃብን ማስወገድ በጋራ ትስስር:
ከጎረቤቶች ጋራ ለመኖር በፍቅር:
ለአፍሪቃ ምሳሌ በዲሞክራሲ ፈር:
ኢትዮጵያን መገንባት ይሁን የኛ ተግባር:
ለዚሁ ሁሉ ታዲያ ሥርዓት እንዲኖር:
ከሥሩ መናድ ነው የወያኔን አሻጥር:
መተካት ግድ ነው በወገናዊ ፍቅር:
በዋናነት ይታይ ህገ-መንግሥትን መፍጠር:
ሲቪል ህብረተሰብን ማሳደግ ማወቀር:
የሁሉንም ዜጋ መብት የሚያስከብር:
መገንባት ብቻ ነው ሌላ የለው ሚስጢር:
ያየነውት የሰማነው በልባችን ይደር:
ውሸቴም ከሆነ ኦባማ ይመስክር።

♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦ ♦

*♣ ለተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችንም አእምሮ፥ ብርታት፥ ጥንካሬ፥ አርቆ አስተዋይነትና ብልኃት ይስጣቸው።*

*M. Adugna (PhD, PGCE, MSc, BSc) is an expert in the field of **VSAT** Comm. He is a University lecturer and can be reached at sofomore@googlemail.com*